


# የኮሎምቢያ ዲስትሪክት
# የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት

## ዲስትሪክቱ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን መታገል ይችል ዘንድ እንዴት መርዳት ይችላሉ?

### *ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ምንድን ነው?*

ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በዚህ ዘመን የሚታይ የባርነት ዓይነት እና ከባድ ወንጀል ነው። ህገወጥ አዘዋዋሪዎች የህገወጥ ተግባሩ ሰለባዎች በጉልበት ሥራ ወይም በወሲባዊ ንግድ ብዝበዛ እንዲሳተፉ ለማድረግ ኃይል፣ ማጭበርበር፣ ወይም ማስገደድ ይጠቀማሉ።

በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ያሉ የራሳችን ሰፈሮች ጨምሮ፣ በመላው ዓለም በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በህገወጥ መንገድ ይዘዋወራሉ። ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ከሕገወጥ የአደንዛዥ እጽ ዝውውር ቀጥሎ በዓለም ላይ ሁለተኛው ትልቁ እና በፍጥነት እያደገ ያለ የወንጀል ኢንዱስትሪ ነው። የሚከተሉት አንዳንድ ጠቃሚ እውነታዎች ናቸው፥

- ከሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች መካከል ግማሽ ያህሉ ልጆች ናቸው። እንዲያውም፣ አንድ ወጣት ሰው በህገወጥ የወሲብ ንግድ ላይ የሚገባበት አማካይ ዕድሜ 12 ዓመት ነው። ተጠቂው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ከሆነ፣ ህገወጥ ዝውውር መሆኑን ለማረጋገጥ ምንም ዓይነት ኃይል፣ ማጭበርበር፣ ወይም ማስገደድ መጠቀም አስፈላጊ አይደለም። አንድ በወሲብ የንግድ ድርጊት ላይ እንዲሳተፍ የሆነ እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ወጣት የህገወጥ ዝውውር ሰለባ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል።

- የወሲብ ህገወጥ አዘዋዋሪዎች ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች በተለይም ወጣቶች ላይ የሚያነጣጥሩ ሲሆን፣ አብዛኛውን ጊዜም ለመንከባከብ፣ ፍቅር ለመስጠት፣ ወይም ጀብዱ የተሞሉ ተስፋዎችን በመስጠት ያባብሏቸዋል። ተጠቂዎቹን በማኅበራዊ ድህረ ገጾች በኩል ያጠምዷቸዋል ወይም በክለቦች እና ቡና ቤቶች፣ በትምህርት ቤት፣ በገበያ ማዕከሎች ውስጥ ወይም በባቡር ጣቢያዎች አካባቢ ሊቀርቧቸው ይችላሉ።

- ህገወጥ የሰራተኛ ዝውውር ዕዳን ለመክፈል የጉልበት ስራ መስራትን፣ የግዳጅ የጉልበት ሥራ፣ እና በፍቃደኝነት ያልሆነ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ሁኔታዎችን ያካትታል። የተለመዱ ህገወጥ የሰራተኛ ዝውውር ዓይነቶች ሰዎች ኢሰብዓዊ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እና በጣም ትንሽ በሆነ ወይም ያለ ምንም ክፍያ የቤት ሰራተኞች እና የፋብሪካ ሠራተኞች ሆነው የሚሰሩ ሰዎችን ያጠቃልላሉ።

- የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች በመረበሻቸው ወይም በድንጋጤ ስሜት ውስጥ በመሆናቸው፣ በአካላዊ ጥቃት፣ በቤተሰቦቻቸው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በመፍራት፣ ሌላ መሄጃ የሌላቸው በመሆኑ፣ ባለሥልጣናትን ባለማመናቸው ምክንያቶች ብዙውን ጊዜ ነገሩን ገሃድ አውጥተው ለመናገር እና ህገወጥ አዘዋዋሪዎችን ትተው ለመሄድ አይችሉም።

የሰዎች ህገወጥ ዝውውር ምልክቶችን ለመለየት ከቻሉ፣ የሰው ሕይወት ለማዳን ሊረዱ ይችላል።

### *ቀይ ባንዲራ እና የማስጠንቀቂያ ምልክቶች*

ልጆችን ለወሲብ መሸጥ በመላው ዓለም የሚፈጸም ክስተት ሲሆን፣ በሚያሳዝን ሁኔታ እዚሁ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥም ይከሰታል። እርስዎም የሰዎች ህገወጥ ዝውውር ምልክቶችን ለመለየት ከቻሉ፣ የአንድን ሰው ሕይወት ለማዳን ሊረዱ ይችላል።

### *ለመርዳት ምን ማድረግ ይችላሉ?*

ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ምልክቶችን በንቃት ይከታተሉ። ምልክቶች ካዩ፣ የተጠረጠሩ ህገወጥ አዘዋዋሪዎቹን ወይም ተጠቂዎችን ለመጋፈጥ አይሞክሩ፣ ይልቁንም እባክዎትን ሁኔታውን ለሚመለከታቸው ባለስልጣናት ይግለጹ።

እርስዎ ወይም የሚያውቁት ሰው የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ ከሆነ እርዳታ ለማግኘት፥

- ወደ **ብሔራዊ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር መስመር፥ በስልክ ቁጥር 1-888-373-7888 ይደውሉ**
- ወይም **"Help" የሚለውን ጽሁፍ ወደ 233733 ይላኩ (ነጻ ይሁኑ)።**

በፍትህ ለህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች አዋጅ መሰረት፣ የልጆች ወሲባዊ ብዝበዛ አንድ የልጆች ጥቃት ዓይነት ነው። በኮሎምቢያ ዲስትሪክት

ህገወጥ የወሲብ ንግድ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- ከቤት ጠፍቶ መሄድ ወይም መሸሽ፤
- ከትምህርት ቤት መቅረት፤
- እራሳቸው ያልገዙትን ተንቀሳቃሽ ስልክ መያዝ፤
- የራሳቸው ባልሆኑ ክሬዲት ካርዶች ግዢዎችን መፈጸም፤
- በእድሜ ከፍ ያሉ ፍቅረኞች፤
- እንደ የመቃጠል ምልክቶች፣ የሰውነት መበለዝ፣ ወይም ቁስል የመሳሰሉ የአካላዊ ጥቃት ምልክቶች፤
- አዳዲስ ንቅሳቶች (ህገወጥ አዘዋዋሪዎች ብዙውን ጊዜ እንደ መለያ ምልክት ንቅሳቶችን ይጠቀማሉ)፤
- ከዱርዬዎች ቡድን ጋር የቀረቤታ ምልክቶች።

የሰራተኛ ህገወጥ ዝውውር የማስጠንቀቂያ ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- የማይከፈልበት፣ በጣም ትንሽ የሚከፈልበት፣ ወይም በጉርሻ መልክ ብቻ የሚከፈል፤
- ከመጠን በላይ ለረጅም ጊዜ ወይም ባልተለመዱ የስራ ሰዓታት መስራት፤
- እንደፈለጉ ከስራ ቦታ ወጥቶ መሄድ ወይም መምጣት አይችሉም፤
- ከፍተኛ እዳ የሚኖርባቸው ሲሆን ለመክፈል አይችሉም፤
- እንደ ፓስፖርት/የደህንነት ካርድ ያሉ ሰነዶች ይይዛሉ፤ እና
- በስራ ወይም በመኖሪያ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ የደህንነት ሁኔታዎች ይኖራሉ (ለምሳሌ፥ የማያሳይ መስታወት ያላቸው መስኮቶች፣ ባለ እሾህ ሽቦ አጥር፣ የደህንነት ካሜራዎች፣ ወዘተ)

ውስጥ ሊከናወን ስለሚችል የሕጻናት ህገወጥ ዝውውር ሁኔታ በተመለከተ መረጃ አለኝ ብለው የሚያምኑ ከሆነ፥

- **የልጆች ጥቃት እና ቸል ማለት መስመር** በስልክ ቁጥር **202-671- SAFE (7233) ይደውሉ።**

## *የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት (OAG) የህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመዋጋት ምን እያደረገ ነው?*

የኦ.ኤ.ጂ *(OAG)* ጠበቃዎች በተለይ በልጆች ደህንነት እና የወጣት ፍትህ ስርዓቶች *(Child Welfare and Juvenile Justice systems)* ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶች ለህገወጥ የወሲብ ንግድ የተጋለጡ መሆናቸውን የሚያውቁ ሲሆን፣ ወሲብን በገንዘብ፣ በምግብ፣ በመጠለያ፣ በልብስ እንዲቀይሩ የተገደዱ የጥቃት ሰለባዎችን በመወከል ሠርተዋል። ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ራሲን በከተማ አቀፍ ትብብር እና የመከላከል ትምህርት በማድረግ ይህንን ጉዳይ ቅድሚያ ሰጥተውታል።

በኦ.ኤ.ጂ *(OAG)* ውስጥ ያለው የሕዝብ ደህንነት እና የቤተሰብ አገልግሎቶች መምሪያ በወሲባዊ ንግድ ብዝበዛ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ፣ ወይም ለመሳተፍ አደጋ የተጋለጡ ወጣቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በሚገመግም ከተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የተውጣጡ ተሳታፊዎች ባሉበት ቡድን ውስጥ ይሳተፋል። ቡድኑ እያንዳንዱን ጉዳይ ለመገምገም በወር አንድ ጊዜ የሚገናኝ ሲሆን እንደ የህክምና ምርመራ፣ የአእምሮ ጤንነት አገልግሎቶች እና የድጋፍ ቡድኖች ያሉ አገልግሎቶችን ይመክራል። ይህ ትብብር የህገወጥ ዝውውር ሰለባ የሆኑ ወጣቶች ተለይተው መታወቃቸውን እና እርዳታ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል።

በተጨማሪም የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት የሰዎች ህገወጥ ዝውውር ውስጥ ተሳትፎን ለመከላከል እና ይህንን ህገወጥ ዝውውር በተመለከተም ሪፖርት ማድረግን ለማበረታታት ማህበረሰቦችን በማስተማር እና በወጣቶች ዘንድም ተደራሽ ለመሆን ጥረቱን እያስፋፋ ነው።


የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤትን ለማነጋገር፥
441 4th Street, NW, Washington, DC 20001
ስልክ፥ (202) 727-3400 ፋክስ፥ (202) 347-8922 TTY: (202) 727-3400
ኢሜይል፥ dc.oag@dc.gov